ላይ ያሉ የአፕላይድ ሳይንስ ተመራቂዎች የትምህርት ጥራትን ቅድሚያ ከመስጠት አንፃር ከመምህርነት ሙያ እንዲወጡ ተደርጎ ወደ ድጋፍ ሰጭ ስራ የሚሰማሩበት አግባብ ይመቻቻል።

4.3 የክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች የድግሪ መምህራን ፍላጎት እንደሚኖራቸው ሲያረጋግጡ በአፕላይድ ሳይንስ የትምህርት መስክ የሰለጠኑና ከፍተኛ ውጤት ያላቸውን ተመራቂዎች በመመልመል ቀድመው የ1 ዓመት (10 ወር) የማስተማር ሙያ ስልጠና ከአሰልጣኝ ዩኒቨርስቲዎች ጋር ውል በመፈፀም ማስተማር ሙያ ስልጠና ማኑዋል መሰረት አሰልጥኖ ወደ ማስተማር ስራ ማስገባት እና ጥቅማጥቅማቸውን በደረጃ እድገት መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

4.4 የክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች በከፍተኛ በመምህራን እጥረት የተነሳ የማስተማር ሙያ ስልጠና ሳይወስዱ በማስተማር ስራ የሚሰማሩ የአፕላይድ ሳይንስ ምሩቃን የሚቀጠሩበት ሁኔታ ከተፈጠረ የደሞወዝ መጠን ከላይ በቁጥር 1.1 በተገለፀው መሠረት የሚስተናገዱ ይሆናል።

4.5 የማስተማር ሙያ ስልጠና ሳያጠናቅቁ ለአንድ ግዜ ብቻ ትይዩ የደረጃ እድገት የተፈቀደላቸው የአፕላይድ ሳይንስ ተመራቂዎች ወይም የትምህርት ደረጃቸውን ያሻሻሉ/የሚያሻሽሉ ነባር መምህራን ለቀጣይ የደረጃ እድገት መወዳደር የሚችሉት ሥልጠናውን ስለ ማጠናቀቃቸው ማስረጃ ማቅረብ ሲችሉ ብቻ ነው።

የተፈጻሚነት ጊዜ

ይህ ውሳኔ ከነሐሴ 1ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።